**የኢመርጀንሲ አሲስታንስ (ኢ.ኤ) የተመሳሳይ መጠላ ፕሮግራም ህጎች አጭር ማብራሪያ**
**ጃንዋሪ 2015 እንደተሻሻለ - መጠለያ**

**ማስታወሻ፡-** ይህ የተመሳሳይ መጠለያ ፕሮግራም ህጎች (ህጎች) አጭር ማብራሪያ ነው። ለዝርዝሩ፣ ሙሉውን ተመሳሳይ የመጠለያ ፕሮግራም ህጎች ይመልከቱ። ሙሉው ህግ ሁሉንም ነጥቦች የያዘ ነው። ሁሉንም ዝርዝር ለመረዳትና መብትና ግዴታዎችዎን ለማወቅ ይህን አጭር ማብራሪያና ሙሉ ህጉን ማየት ይኖርብዎታል። ይህ ህግ በጠጋጉ መጠለያዎች፣ በሆቴሎች ወይም በተበታተኑ የጣቢያ ክፍሎች የሚኖሩ ቤተሰቦችን ይመለከታል። የህጎችዎን ቅጂ መያዝና ህጎችን መረዳት የእርስዎ ሃላፊነት ነው።

**ማስጠንቀቂያ፡-**

- ሁሉንም ህጎች ካልተገነዘቧቸው፣ የዲ.ኤች.ሲ.ዲ ሰራተኛዎን ወይም ሌላ የሚያምኑት ሰው እንዳብራራልዎ ይጠይቁ።
- በጠቅላላ ሦስት ህጎችን ከጣሱ ከዚህ መጠለያ ሊባረሩ ይችላሉ።
- የተወሰኑ የህግ ጥሰቶች «በቂ ምክንያት» የሚኖራቸው ከሆነ ይቅርታ ሊሰጥባቸው ይችላል፣ ነገር ግን፣ ማንኛውም ጥሩ ምክንያት «በቂ ምክንያት»ላይሆን ይችላል። ምን ምን ነገሮች እንደ «በቂ ምክንያት» እንደሚቆጠሩ ለማይት ሙሉ ህጎችንና የዲ.ኤች.ሲ.ዲ ድንጋጌዎችን ይመልከቱ።
- ከኢ.ኤ ፕሮግራም ተባረው ከሆነ፣ እርስዎ እና ልጆችዎ ለ12 ወራት እንዳይመለሱ ተከልክለው ሊሆን ይችላል።

1. **ወደ ክፍሎች መግባት/መፈለግ** – የመጠለያና የሆቴል ሰራተኞች ደህንነቱና ንፅህናው የተጠበቀ ክፍል ሆኖ መቀጠሉን ለማረጋገጥ ከ24 ሰዓት በፊት አስቀድመው በማሳወቅ የእርስዎን ክፍል ቀጣይነት ባለው ሁኔታ የመጎብኘት መብት አላቸው። ህጎችን እየጣሱ እንደሆነ መጠራጠርን ጨምሮ አስቸኳይ ሁኔታ በገጠመ ጊዜ ሰራተኞች አስቀድመው ሳያሳውቁ ክፍልዎን ሊፈትሹ ይችላሉ። ሰራተኞቹ ለፍተሻ ወደክፍለዎ ከመግባታቸው በፊት ሊያንኳኩና እራሳቸውን ሊያሳውቁ ይገባል። ሆቴል ውስጥ፣ በየቀኑ ለሦስት ሰዓታት በቀን የክፍል ማስተካከል ስራ እንደሚሰራ ተነግሮዎት ከሆነ ይህ ማስተካከል ስራ እንዲሰራ መፍቀድ አለብዎ። በህመም ምክንያት በተከታታይ ከሦስት ቀን በላይ የማስተካከሉን ስራ እንዳይሰራ ሊከለክሉ አይችሉም።

2. **የልጅ /የህፃን እንክብካቤ** – በመጠለያ ወይም በሆቴል የልጅ እንክብካቤን ይመለከታል።
   *በተጠጋጋ መጠለያ የሚኖሩ ከሆነ* — ሌላ የመጠለያ ነዋሪ ልጅዎን (ልጆችዎን) ሊነከባከብልዎ ይችላል፣ ነገር ግን ይህ የሚሆነው የመጠለያ ሰራተኛ አስቀድሞ ከፈቀደ በኋላ ወይም ደግሞ በበቂ ምክንያት፣ ለምሳሌ በአደጋ ጊዜ ብቻ ነው።
   *ሆቴል ውስጥ ከሆኑ፣* — በተመሳሳይ ሆቴል ውስጥ የሚኖር ሌላ የኢ.ኤ ተሳታፊ ልጆችዎን ሊንከባከብ የሚችል ሲሆን ይህን ለማድረግ ግን ከዲ.ኤች.ሲ.ዲ በቅድሚያ ፈቃድ በማግኘት በበቂ ምክንያት፣ ለምሳሌ በአደጋ ጊዜ መሆን አለበት።
   *በመጠለያውም ሆነ በሆቴሎች* — 14 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነው(ናት) ልጅ እራሱን/እራሷን ወይም ታናናሽ የቤተሰብ አባላትን መንከባከብ የሚችሉ ሲሆን ይህን ሊያደርጉ የሚችሉትም አስቀድመው ፈቃድ ካገኙ

ወይም ደግሞ በቂ ምክንያት ሲኖር፣ ለምሳሌ በአደጋ ጊዜ ብቻ ነው። የልጅ እንክብካቤው በእርስዎ ክፍል ውስጥ ወይም በልጅ መንከባከቢያ ክፍል ውስጥ ወይም ታዳጊ ህፃናትን ወደመጠለያና ወደሆቴል ወይም በተቃራኒው በሚጓጓዙበት ጊዜ ወደ ትራንስፖርት ሲያደርሱ መሆን አለበት። **የልጅ እንክብካቤ ፈቃድ ለማግኘት መጠየቂያ ቅፅ በመጠለያው ወይም በሆቴሉ መግቢያ ይገኛል።** የልጅ እንክብካቤው ለአንድ ቀን፣ ለበርካታ ቀናት ወይም ቀጣይነት ያለው ሊሆን ይችላል።
ፈቃዱ ቢያንስ ከሁለት የስራ ቀናት በፊት መጠየቅ አለበት። ከሁለት ቀናት በፊት አስቀድመው ለመጠየቅ የማይችሉ ከሆነ፣ ፈቃዱን መጠየቅና ለምን አስቀድመው መጠየቅ እንዳልቻሉ ማስረዳት አለብዎ። ለልጅ እንክብካቤ ቢያንስ ከ2 ቀናት በፊት ጠይቀው ከነበረ ነገር ግን ምንም ምላሽ ካላገኙ፣ ጥያቄዎ ተቀባይነት አግኝቷል።

3. **ጥንቃቄ ለልጆች –** በኢ.ኤ ቤተሰብ ለሚኖሩ ልጆች፣ ትምህርት ቤት መከታተላቸውን ማረጋገጥና በአግባቡ ምግብ ወስደው ረፍት እንዲያገኙ ማድረግን ጨምሮ፣ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ የጎልማሳ የቤተሰብ አባላት ሃላፊነት ነው።

4. **ልጅን ብቻውን(ዋን) መተው –** በማንናውም ጊዜ ልጆችን ለብቻቸው መተው አይችሉም። **ይህ ማለት በአጠቃላይ ፈቃድ ከተሰጠው ተንከባካቢ ጋር ካልሆኑ በስተቀር** ልጆችዎ ትንሽ ጊዜም ቢሆን ያለእርስዎ ሊሆኑ፣ ከአይንና ከጆሮዎ ሊርቁ አይገባም። 16 ዓመት የሆነው(ናት) ልጅ እራሡን(ሧን) ለመንከባከብ የተፈቀደለት (ላት) ከሆነ ወይም ጎልማሳ እንክብካቤ አድራጊ በቅጥር ግቢው ውስጥ ካለ ወይም በስልክ ወይም በአካል ሊገኝ የሚችል ከሆነ ልጁ(ጅቷ) በሆቴሉ የጋራ መገልገያ አካባቢ ሊንቀሳቀስ(ልትንቀሳቀስ) ይችላል(ትችላለች)።

5. **የምሽት ገደብ –** በዲ.ኤች.ሲ.ዲ እንደተገለፀው በቂ ምክንያት ከሌለዎት በስተቀር፣ በተቀመጠው የምሽት ገደብ ሰዓት ወደመጠለያው ወይም ወደ ሆቴሉ መመለስ አለብዎት። በመጠለያው ወይም በሆቴሉ ከተቀመጠው የሰዓት ገደብ አንስቶ እስከሚቀጥለው ጠዋት 6 ኤ.ኤም ድረስ በክፍልዎ እንዲገኙ የሚጠይቀውን ህግ ማክበር አለብዎት (ብዙ ጊዜ የምሽት ገደቡ ካለፈ ጀምሮ ባለው አንድ ሰዓት ውስጥ) በስራዎ ፀባይ ወይም በሌላ በህጎች ላይ የተገለፁ ህጎች መነሻነት የሚገቡበትን የምሽት ሰዓት ገደብ ማስተካከል ይችላሉ። ከምሽት ገደቡ በአንድ ሰዓት ቀድሞ የሚጀምረውን «የፀጥታ ጊዜ» ማክበር አለብዎ።

6. **በንብረት ላይ የሚደርስ ጉዳትና ወጪዎቹ –** የመጠለያ ወይም የሆቴል ንብረት ማውደም አይችሉም። የመጠለያ ወይም የሆቴል ንብረት ላይ ጉዳት ካደረሱ ወይም ካንቀሳቀሱ፣ ለደረሰው ጉዳት እንዲከፍሉ ሊገደዱ ይችላሉ። እንዲሁም በኢ.ኤ የመጠለያ ፕሮግራም የማይሸፈኑ እንደ የስልክ ወጪና የፊልም ኪራዮች የመሳሰሉትን ወጪዎች መሸፈን አለብዎ። ምክንያታዊ የሆነ መልሶ የመክፈል እቅድ ካለዎ፣ በመጠለያው ወይም በሆቴሉ ንብረት ላይ ጉዳት የማድረስ ህግ ጥሰት አይኖርብዎትም።

7. **በዲ.ኤች.ሲ.ዲ የሚጠይቀው –** ከመጠለያ ሰራተኞች፣ ከዲ.ኤች.ሲ.ዲ ሰራተኞች፣ ከቤት ፍለጋ ሰራተኞች ወይም ከሌሎች ከዲ.ኤች.ሲ.ዲ ጋር በስምምነት ከሚሰሩ ኤጀንሲዎች ጋር በሚኖር ስብሰባ ላይ መሳተፍ አለብዎ። በተጨማሪም ቤት ለማግኘት ያለውን እቅድ ማክበር አለብዎት፣ ይህም አሁን ያለብዎን ትዕዛዝ የትዕዛዝ

ማስታወቂያው በደረሰዎ በ30 ቀናት ውስጥ መፍታትንም ያካትታል። በተመደቡበት ቀን ከ8 ፒ.ኤም በፊት ከመጠለያው ወይም ከሆቴሉ መድረስ አለብዎት። የቀጠሮውን ቀን ለመቀየር ከፈለጉ ለማነጋገር የሚያስፈልግዎትን መረጃ ሰራተኛ ይሰጥዎታል።

8. **የፀጥታን ደስታ መረበሽ –** ሌሎች የመጠለያ ቤተሰቦችን፣ በተበታተነ ጣባ አፓርትመንት ግንባታዎች የሚኖሩ ሌሎች ነዋሪዎችን፣ ወይም ሌሎችን የሆቴል እንግዶችን በእጅጉ በሚረብሽ ተግባር መሳተፍ አይቻልም።

9. **የአደንዛዥ እፅ ምርመራ –** መጠለያው ለአደንዛዥ እፅ ምርመራው የሚከፍል ከሆነ፣ እንዲሁም እርስዎ መድሃኒትን ያላግባብ እየተጠቀሙ እንደሆነ ጥርጣሬ የሚያሳድር እርስዎን የተመለከተ ምክንያት እንዳለው መጠለያው በፅሁፍ ካሳወቀዎ፣ የአደንዛዥ እፅ ምርመራ ማድረግ አለብዎ።

10. **የእሳት ደህንነትና ማጨስ –** ማጨስ፣ ማንኛውንም እሳት ሊያስነሱ የሚችሉ ነገሮችን መጠቀም (ሻማዎችን፣ እጣን፣ ፈቃድ ያልተሰጣቸው ማብሰያዎችን ጨምሮ)፣ እንዲሁም በማንኛውም መጠለያ ወይም ሆቴል ውስጥ ጭስ የሚስጠነቅቁ መሳሪያዎችን እንዳይሰሩ ማድረግ አይቻልም። ከመጠለያው ወይም ከሆቴሉ ውጪ ለማጨስ በተፈቀደ ቦታ ብቻ ያጭሱ።

11. **የሚያስጨንቁ ወይም የሚያስፈራሩ ቃላት –** በሌሎች የኢ.ኤ ነዋሪዎች ወይም በሆቴል እንግዶች፣ በአገልግሎት አቅራቢዎች፣ ወይም በዲ.ኤች.ሲ.ዲ፣ በመጠለያ ወይም በሆቴል ሰራተኛ ላይ የሚያጨንቁ ወይም የሚያስፈራሩ ቃላትን መጠቀም አይችሉም።

12. **ህገወጥ እንቅስቃሴ –** በመጠለያው ወይም በሆቴሉ አካባቢ ማንኛውንም የግዛት፣ የፌደራል ወይም የአካባቢ ህጎች የሚጥስ ማንኛውም እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው።

13. **ህጋዊ ጉዳዮች –** ለኢ.ኤ ሰራተኞች እና ለዲ.ኤች.ሲ.ዲ ሰራተኞች አሁን ስላሉ ማዘዣዎች፣ የሚከለክሉ ትዕዛዞች እንዲሁም ሌሎች የፍርድ ቤት ትዕዛዞች በተመለከተ መረጃ መስጠት አለብዎ። እነዚህን በሂደት ላይ ያሉ ህጋዊ ጉዳዮች የመፍቻ መንገድ ቤት ለማግኘት ባለው እቅድ ውስጥ ተካቷል።

14. **ሌሊት ውጭ ስለማደር –** እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል በኢ.ኤ በተመደበበት (መጠለያም ይሁን ሆቴል) ማደር አለበት፣ ከዲ.ኤች.ሲ.ዲ በቅድሚያ ፈቃድ ካልተሰጠ ወይም በቂ ምክንያት ለምሳሌ በአደጋ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር። ፈቃድ በመጠየቅ ቤተሰብዎ በወር ውስጥ ለአራት ሌሊቶች በኢ.ኤ ከተመደበበት ውጭ ሊያድር ይችላል። ከመጠለያው ወይም ከሆቴሉ ውጭ ፈቃድ በማግኘት ለማደር የሚሞላው ቅፅ ከመጠለያው ወይም ከሆቴሉ መግቢያ ላይ ይገኛል። ፈቃዱ ቢያንስ ከሁለት የስራ ቀናት በፊት መጠየቅ አለበት። ከሁለት ቀናት በፊት አስቀድመው ለመጠየቅ የማይችሉ ከሆነ፣ ፈቃዱን መጠየቅና ለምን አስቀድመው መጠየቅ እንዳልቻሉ ማስረዳት አለብዎ። አጠቃላይ ቤተሰቡ በተከታታይ ከአራት ቀናት በላይ ውጭ ለማደር ቢፈልግ የዲ.ኤች.ሲ.ዲ ቤት አልባ

አስተባባሪዎን ጊዛዊ የአደጋ ጊዜ መጠለያ መቋረጥ (ቲ.ኢ.ኤስ.አይ) ይጠይቁ። ውጭ ለማደር ቢያንስ ከ2 ቀናት በፊት ጠይቀው ከነበረ ነገር ግን ምንም ምላሽ ካላገኙ፣ ጥያቄዎ ተቀባይነት አግኝቷል።

15. **የግል ንብረትና የክፍል ንፅህና** – ክፍልዎን ንፁህና የተስተካከለ አድርገው መያዝ አለብዎ። በማንኛውም የተጠጋጋ ወይም የተበታተነ መጠለያ ውስጥ ለእያንዳንዱ አባል ሁለት የቆሻሻ መጠቅለያዎች በላይ ሊሆን የሚችል ንብረት ሊኖረው አይችልም። ከዚህ በላይ ንብረት ይዘው ወደ መጠለያው ከመጡ፣ ተጨማሪ ንብረቶችን ለማስወገድ 7 ቀናት ይኖርዎታል።

16. **የቤት እንስሳት** – ምንም የቤት እንስሳት በመጠለያው ወይም በሆቴል ቅጥር ውስጥ ሊኖርዎ አይችልም፣ የተመዘገቡ የአገልግሎት እንስሳት ካልሆኑ በስተቀር።

17. **የታዘዙ መድሃኒቶች** – የታዘዙ መድሃኒቶችን በአግባቡ ማስቀመጥና መውሰድ እንዲሁም መድሃኒቶቹ በህፃናትና በሌሎች ያልታዘዘላቸው ሰዎች እንዳይወሰዱ ማድረግ የእርስዎ ሃላፊነት ነው። በመጠለያ ቦታ፣ የመጠለያ ሰራተኛ መድሃኒትዎን በአስተማማኝ ቦታ ለማስቀመጥ ሊረዳዎ ይገባል። ሆቴል ውስጥ፣ መድሃኒትዎን በአስተማማኝነት የሚያስቀምጡበት ቦታ ሆቴሉ እንዲያዘጋጅልዎ በፅሁፍ መጠየቅ ይችላሉ። አስተማማኝ ማስቀመጫ ከሌለዎ፣ መድሃኒቱን በጥሩ ሁኔታ ለመያዝ የተቻለውን ሁሉ ማድረግ አለብዎ።

18. **ፆታዊ ጠቃት** – በመጠለያው ወይም በሆቴሉ ውስጥ በማንኛውም ሰው ላይ ፆታዊ ጥቃት ማድረስ የተከለከለ ነው።

19. **የተከለከሉ ነገሮችን መጠቀም** – በመጠለያ ወይም በሆቴል ውስጥ አልኮል ወይም ሌላ ቁጥጥር ያለባቸውን ነገሮች መያዝ ወይም መጠቀም ክልክል ነው። ያልተከፈተ የአልኮል ጠርሙስም ቢሆን ይዞ መገኘት የተከለከለ ነው። አልኮል ወይም ሌላ የተከለከለ ነገር ከጣቢያው ውጪ መጠቀም፣ በመጠቀምዎ በመጠለያው ወይም በሆቴሉ ውስጥ ችግር እንዲፈጥሩ የሚያደርግ ከሆነ፣ የተከለከለ ነው።

20. **ነውጠኛ ባህሪ፣ ህፃናትን መበደል ወይም ትኩረት መንፈግ** – በማንኛውም የነውጠኝነት ባህሪ ማንፀባረቅ ወይም ህፃናትን መበደል ወይም ትኩረት አለመስጠት የተከለከለ ነው። ልጆችዎን አካላዊ ቅጣት መቅጣት እንደመበደል ወይም ትኩረት እንደመንፈግ ይቆጠራል።

21. **ጎብኝዎች/እንግዶች** – የመጠለያ ህጉን በማክበር ጎብኚዎች በመጠለያው ሊኖሩዎ ይችላል። እውቅና ያለው የማህበራዊ አገልግሎቶች አቅራቢ ወይም በሆቴሉ ውስጥ የሚኖር የቤተሰብ አባል ካልሆነ በስተቀር ሆቴል ውስጥ ጎብኝዎች ሊኖሩዎት አይችሉም። በሆቴሉ ውስጥ የሌሎች ቤተሰብ አባላት ጉብኝት ሊያደርጉ የሚችሉት የቤተሰብ አባል የሆነ ጎልማሳ ሰው በክፍሉ ውስጥ ካለ ወይም በሆቴሉ ውስጥ ካለና በስልክ ወይም በድምፅ ጥሪ ሊገኝ የሚችል ከሆነ፣ ወይም ለሌላ ቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ለማድረግ ፈቃድ ያለዎት ከሆነ ብቻ ነው። እንግዶች የሚጎበኙ ከሆነ፣ በሆቴሉ አንድ ክፍል ውስጥ ከ6 ግለሰቦች በላይ በአንድ ጊዜ ሊገኙ አይችሉም። በመጠለያው

ወይም በሆቴሉ የጋራ መገልገያ አካባቢ ጎብኚዎች መቼ እና የት ሊጎበኙዎ እንደሚችሉ የመጠለያ ወይም የሆቴሉን ህጎች ማክበር አለብዎ።

22. **የጦር መሳሪያዎች** – በመጠለያው ወይም በሆቴሉ ቅጥር ግቢ ውስጥ ምንም አይነት የጦር መሳሪያ መያዝ አይፈቀድም። ምንም እንኳን በህጋዊነት የተመዘገቡ ቢሆኑም የጦር መሳሪያዎች ፈፅሞ አይፈቀዱም።

ከተመሳሳይ የመጠለያ ፕሮግራም ህጎች በተጨማሪ መጠለያው ወይም ሆቴሉ የእራሱ የሆኑ ህጎች ሊኖሩት ይችላል። በመጠለያው ወይም በሆቴሉ የወጡ ህጎችን መጣስ እንደ ጥሰት ሊያዝ ወይም እንዲባረሩ ሊያደርግ ባይችልም፣ ወደሌላ ቦታ እንዲዛወሩ ወይም የተወሰኑ ጥቅማጥቅሞችን እንዲከለከሉ ሊያደርግ ይችላል። ሁሉንም ህጎች ለማክበር መሞከር አለብዎት።

እነዚህ ህጎች ምን ማለት እንደሆኑ ጥያቄ ካለዎት፣ የዲ.ኤች.ሲ.ዲ ቤት-አልባ አስተባባሪዎን መጠየቅ አለብዎ። በመጠለያ ውስጥ፣ የመጠለያ ሰራተኛ መጠየቅም ይችላሉ። በሆቴሉ ውስጥ፣ የሽግግር የቤት-አልባ አስተባባሪውን፣ ኤፍ.ኦ.አር የቤተሰብ ጎብኚ፣ የኢ.ኤ ሆቴል ድጋፍ ሰራተኛ ወይም የሆምቤዝ ሊያዞን ሊያነጋግሩ ይችላሉ።

ይህ አጭር ማብራሪያ ለኢ.ኤ ተሳታፊዎች እና ለፕሮግራም ሰራተኞች ቀላል እንዲሆን ታስቦ የተዘጋጀ ነው። ነገሮችን በድፍረትና በቀላል አቀራረብ የያዘ ስለሆነ ሙሉ ህጎችን ለመተርጎም ወይም ለማሟላት አገልግሎት ላይ መዋል የለበትም። በዚህ አጭር ማብራራና ሙሉ ህጎችን በያዘው ሰነድ መካከል የአገላለፅ ልዩነት ከተፈጠረ፣ ሙሉ ህጎችን የያዘው ቋንቋ ተግባራዊ ይደረጋል።